**ትግላችን መራራ ቢሆንም፣ግብአችን ዕሩቅ አይሆንም!!(ዳዊት ተመስገን,ከኖርዌ )**

04 February 2018

እንናገራለን እንጂ አንማታም የሀገር ፍቅር ከሰዎች ፍቅርና ከሰው ሰውኛ ጉዳዮች ይነጥላል እንዴ?የህወሓት አካል የሆኑት የኦህዴድና የብአዴን ሞግዚቶች ስለ ኢትዮጵያ አንድነት ስብከት የጀመሩት ትንሽ ሰነባብቷል።ሰውየው ከአነጋገሩ ክትነትና ከሚሰጠው ጣዕመ ምስጢር የተነሳ ሲሰሙትና ሲያዳምጡት ቢውሉ ቢያድሩ አይሰለችም ምክኒያቱም የኢትዮጵያ አንድነት ሲጠራ ደስ ይላል።ነገር ግን ኢትዮጵያን በመጥራት ብቻ ያለ ትግበራ ይሆናል እንዴ?እኔን ግራ የገባኝ ከ27 ዓመት በኃላ የኢትዮጵያ አንድነት የሚለው አባባል ያውም በባህር ዳር ስብሰባ ላይ ለአማራው ሕዝብ ኢትዮጵያዊነት ሲሰብኩ ለቀባሪው አረዱት አይሆንም ብዬ ነው።ሐሰትና ስንቅ እያደር ይቀላል እንዳይሆን እሰጋለሁ ወይም ደግሞ ከእሪያ በግ እንደማይወለድ ሁሉ ከሐሰተኛም ሕልምም ቁም ነገር አይገኝም እንዳይሆን።ጦርነታችሁ ስጋና ደም ሆነው ከሚታዩ ጋር ሳይሆን ከጨለማ ገዢዎች እንጂ እንዳለው የጨለማ ገዢ ከሆነው ከድንቁርና ከውሸት ጋር ከተላበሰው ከህወሓት ግብግብ ገጥሞ ሲያሸንፉ እኛ ያኔ የዓይን ምስክር መሆን እንችላለን።የህወሓት የጋሻ ጃግሬ ሆነው እንዲህ ቢሉን ያስገደዳቸው የሕዝብ ሐብቱ አንድነቱ፣የትውልድ ጉልበቱ ኀብረቱ ስለሆነ ብቻ ነው።በሌላ አነጋገር ህወሓት ሕዝባዊ አመፅ ስለተገደደ እንጂ ምነዋ የአኖሌ ሃውልት ጡት የተሰራበት ቦታ ሄደው ወይም አንቦ፣ወለጋ፣ትግራይ ላይ ነው የኢትዮጵያ አንድነት መስበክ ያለባቸው ምክኒያቱ ኢትዮጵያዊነት የተናነቃቸው እዚህ ክልል ላይ እንጂ ኢትዮጵያዊነት ለአማራው አይሰበክም የምለው።

በእኔ በኩል አመንዝራ ካሏት ብትቆርብም አያምኖት ነው በጣም የሚገርመው ኦህዴድና ብአዴን የሚባሉ የህወሓት ደቀ መዝሙሮች የጎጃምን ሕዝብ በኢትዮጵያዊነት ካላጠመኳችሁ በማለታቸው ምነው ከረፈደ ለማለት ነው።መቼስ ድሮ በአባቶቻችን ጊዜ እንዲህ ይባል ነበር ባሪያ ሦስቱን ነገሮች ካላወቀ ታዝዞ መኖርን አይችልም ዕረፍትንም አያገኝም።እነሱም የሚመራውና የሚቃኘው፣ታማኝነት እንደ ቸር ጠባቂ ሆኖ የሚጠብቀው ተግሣጽ ከመጥፎ ልማድ የሚመልሰው ፍርሃት ናቸው።ባሪያ እየተሰደበ ቢገዛ ይበረታል፣እየተሳደበ ቢገዛ ግን አይበረታም። ይህ አባባል አሁን አይሰራም እነዚህ የህወሓት ሞግዚቶች ኦህዴድም ሆነ ብአዴን የኦሮሞና የአማራውን ሕዝብ አይወክሉም።የኢትዮጵያን ትግል ለማኮላሸት በአገዛዙ ከሚጎዱ ሰዎች ይልቅ በአገዛዙ ምክኒያት የሚጠቀሙ ይባዛሉ ልበል የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል አቅጣጫ ለማሳትና ብሎም ጠላት ወያኔ ትንፋሽ እንዲወስድ የተደረገ አባባል ነው የምለው።አዳዲስ የትግል ስልቶችን በመጀመር ወጣቱ ንቃታቸውና ብቃታቸውን በማቀናበር እንዲሁም በማቀላጠፍ በተለያየ ስልት ጉድ የሚባልላቸውን ሰዎች በታትኖ ምንም ትግሉ አቅም እንሌለው ሰው እንዲኖሩ የሚያደርግ አንድ አስቸጋሪና እጅግ የተለመደ ችግር ቢኖር የትኩረት ችግር ነው።እንደምናውቀው እስከ አፍንጫው ድረስ ዘመናዊ መሣሪያ ታጥቆ የመጣው ጠላት ፋሺስት ኢጣልያ ወራሪ አፈር ግጦ ድል የተመታበትን የዓድዋ ዘመቻን ዘወር ብለን ብናስተውል የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ አካል አንድ አምሳል ሆነው ጠላትን ድል ማድረጋቸው እንገነዘባለን።ምነው ቢሉ እምየ ምንሊክ የክተት አዋጅ ባስነገሩበት ጊዜ ሳያመነታ አፈፍ ብሎ የተነሳው ወገን ቀደም ሲል በተለያዩ ጹሁፎቼ ገልጨዋለሁ።የጀግንነት ባሕርይው በነባራዊነት የደነደነ ስሜቱም ከፍቅረ ሀገር ጋር በእጅጉ የላቀ በመሆኑ ነው።ኢትዮጵያዊ ስሜት ይህ መሆኑ እየታወቀና የገድል ባለቤታቸውንም የማይታበል ሆኖ ሳለ አንዳንድ ጉዳይ ተሰምቶ እንደማይታወቅ እንግዳ ሊሆንብን አይገባም።በእኛ በአሁኑ ጊዜ የሚያሳዝነው በአጭሩ የወደፊት ተመልካችነት ሊኖረን አልቻለም።

ስለዚህ ዘወትር ከራሳችን ይልቅ ወደኃላ ተመልካችና አወዳሽ ነን እዚህ ላይ ልትገነዘቡልኝ የምፈልገው ለትግሉ መስዋዕት የሆኑትን ወይም ኢትዮጵያ ሀገራችንን ላቆዮልን አባቶቻችንን ለማለት ፈልጌ አይደለም የወደፊቱን በጉጉት የምንመለከት የወደፊቱ ብርሃን እንዳይጠፋ የምንባዝን የምንደክም አይደለንም።በትክክል በኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይመረጡ ነገር ግን ህወሓት በሞግዚትነት የሰየማቸው የኢትዮጵያ አንድነት በማለታቸው በጣም ደስ ያሰኛል። እውን ጥላቻን አስወግዶ ከሞግዚትነት ወደ ኢትዮጵያዊነት መጣን ሲሉ እነዚህ ወንበዴዎች ደስ የሚያሰኝ ቢሆንም ነገር ግን በግማሽ እውነታን ይዞ ኢትዮጵያዊ ነኝ ማለት አይቻልም።ህወሓት በበኩሉ ሁሉም በየዘሩ ከረጢት እየተፈላለገ እንዲቋጠር ያልማሰው ስር ያልነቀለው ድንጋይ የለም።ከህወሓት ጋር ተቀናጅቶ የሚኖር በየወቅቱ እየተበረዘና እየተንጋደዱ ቃላትና ንዑስ ሐረጎችን እውነተኛ ትርጉም በማስመሰል የሚንቀሳቀሱትን በሚገባ መረዳት ያለብን ይመስለኛል።በኢትዮጵያዊው ዜጋ ደምና አጥንት የተገነባውን አንድነትና ተዋሕዶ የተዛመደውን ነጥሎ ለማውጣት የማይቻለውን የተፈጥሮ ጀግንነት ለማደስና ስርዓት ለማስያዝ የተሠራ መሆኑን ለመገመት አያዳግትም። እንዳለመታደል ሆኖ ነው እንጂ በእርግጥም ሲያስቡትም ዛሬም ቢሆን ነገ እስከ መጭረሻውም ድረስ አትንኩኝ ባይነት ከኢትዮጵያዊነት ባሕርይ ሊነጠል አይችልም።ብሎም ቢሆን ዘመን እየተቆጠረ ዘመን ሲተካ ይህ ኩሩነትና ሀገር ወዳድነት ባሕርይ ከነባራዊነቱ ፈቀቅ በማለት እንዳያውክ አሁንም ወጣቱ ትውልድ ያባቶቹን ጀግንነት እንዲወርስ ማድረጉ አማራጭ የሌለው ተግባር ነው።በኢትዮጵያ ውስጥ በግፍ በጥይት ተደብድበው የወደቁ ብዙዎች ናቸው፣ነገር ግን በነገረ ሠሪ አንደበት እንደጠፉት ባይሆንም ቅኑ።

ሰዎች ከሚወቅሳቸው ዳኞች ይልቅ የገዛ ህሊናቸው እየወቀሰ የሚያሰቃያቸው እጅግ ብዙ ቢኖሩም።የእውነተኛ ተግባር ምንጩ ኢትዮጵያዊ ማንነት ነው ስለዚህም የምናደርጋቸው ነገሮች እንደየ ሰው ሁኔታ የሚለዋወጡ ከሆነ እነዚህ የምናደርጋቸው ነገሮች ከእውነተኛነት የመነጩ ሳይሆኑ ከጥቅም ከፍርሃት ወይም ከተለያየ የራስ ወዳድነት አመለካከቶች የመነጩ እንደሆኑ ጠቋሚ ነው።አክባሪ ኢትዮጵያዊ ማንነት ያለው ሰው የዘርን የሃብትን የዕውቀትንና የመሳሰሉትን ሁኔታዎች ሳያይ ሁሉንም እኩል ያከብራል።እንቅስቃሴ የሌለው የሌሊት ህልም ቅዠት ነው።እርምጃ የማይወሰድበት የቀን ህልም ደግሞ ድንዛዜ ነው።እውነቱ ይህ ነው አንድ ሰዉ ከእንቅልፉ ሲነቃ ይህንና ያንን አለምሁ ካለ በኃላ ሌላ ህልም ለማለም ተመልሶ የሚተኛ ከሆነ ከቅዠት ያለፈ ኑሮ የለውም።እንዲሁም አንድ ሰው ቀን ቁጭ ብሎ በአይነ ህሊናው እየበረረ ይህንና ያንን ሊያደርግ ራሱን የማየት ልማድ ቢኖረውና ይህ ውስጡ የሚጓጓለት ነገር በወረቀት ሊጽፍ እቅድ ሊያወጣለትና ከአንድ ደረጃ ወደሌላኛው ደረጃ የማይንቀሳቀስ ካልሆነ ይህ ሰው ከድንዛዜ አያልፍም።አንድ ነገር ወደ ጋሃዱ ዓለም ከመምጣቱ በፊት በመጀመሪያ በጽንሱ ሃሳብ ግን ሊጨበጥና ሊደረስበት የሚችለው ሲታቀድበትና ስንንቀሳቀስበት መሆኑን አንዘንጋ ከማንም ያልተበደርከውን አንድን በውስጥህ የበቀለ ጽኑ ፍላጎት ለይተህ እወቀው ከዚያም ፍላጎት አንጻር እቅድን በማውጣት የመጀመሪያውን እርምጃ ተራመድ ብዙ ሳትቆይ ሁኔታህ ሲለወጥ ማየትህ የማይቀር ነው።

በአሁኑ ሰዓት ብዙዎች ስልጣን ላይ ያሉ መዝባሪዎች ዘላቂ የኢትዮጵያን ጥቅም ፋላጊ እንጂ፣ዘላቂ የኢትዮጵያ ወዳጅ አይደሉም።ለአማራው ምንታዌ እንደማይጠቅመው ያውቃል ኢትዮጵያ አንድነት እንጂ የኢትዮጵያዊ ምስጢር በአንድነት ገላጭነት ካልታወቀ በስተቀር መረዳት አይቻልም።የስልጣንና የገንዘብ ሌላው አዕይንተ አዕምሮቸውን በስግብግብነት መንጦላት ጋርዶ፣ዕዝነ ልቡናቸውን በአልጠገብ ባይነት ቡሽ ደፍኖ፣እግሮቻቸውን በምኞት ፈረስ ከኢትዮጵያዊነት አንድነት ለይተዉ ለወያኔ ተገዥነት እራሳቸዉን አሳልፈዉ ሰጥተው ኢትዮጵያዊነት ሲሉን እንዴት ነው በእኛ ውስጥ ታአማኒነት ሊኖራቸው የሚችለው።ስልጣንና ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ስር ነው የሚለው ቃል ተቀይሮ ስልጣንና ገንዘብ የደም ስር ነው በሚለው ብሂል ከተተካ ውሎ አድሯል።ዛሬ በሀገራችን ኢትዮጵያ ከስልጣንና ገንዘብ ከመውደድ የተነሳ ነፍስ ሲጠፋ፣እውነት ተደብቆ ሐሰት ሲነግሥ ማየት አዲስ ነገር አይደለም።የስልጣንና የገንዘብ ፍቅር ያነሆለለው ሰው ስለ ኢትዮጵያዊ አንድነት ነገር የሚያስብበት ጊዜ አለው ብዬ እምነት የለኝም።የድሮ አባቶቻችን ሁለመናቸውን ለሕዝብ ክብርና ለሀገር ፍቅር ሰጥተው የሕዝብን እሮሮ አድማጭና ተግባሪ የሆኑ መሪዎች የበቀለባት በኢትዮድያ የታሪክ ገጾች ላይ ሰፍሮ ይገኛሉ።

የኢትዮጵያን ሕዝብን እስከ መቼ ማታለል ይቻላል ኦህዴድና ብአዴን የህወሓት ሞግዚቶች ናቸው እንጂ ምንም ሊያመጡ አይችሉም።ከሞግዚትነት ወደ ኢትዮጵያዊነት ለመምጣት ማሰባቸው ባይከፋም ነገር ግን እነሱ እራሳቸውን ከህወሓት አግልለው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎራ ሆነው አረንጓዴ፣ቢጫ፣ቀይ ሰንደቅ ባንዲራችንን ለብሰው እስካልቆሙ ድረስ የሕዝባዊ አመጹን ለማዳከም የሚያደርጉት ሴራ ጉዞአችን መራራ ግብአችንን ዕሩቅ አያደርገውም።ሮበርት ሙጋቤ ጊዜ ነው እንጂ ቁም ነገራም፣ኖርኩኝስ ማለት አያኮራም ሲል አልሰሙትም እንዴ።ማንም የህወሓት አሽከር እንዲህ ነው እንዲያ ነው ሲለን ለውጥ ይመጣል ብለን ካሰብን ማስተዋል ተስኖናል ማለት ነው።ውኃ ተመልሶ ወደ ኃላው ቢሄድ(ቢፈስ) ዎፎች አለ ክንፍ ቢበሩ፣ቁራ እንደበረዶ ቢነጣ ህወሓት አዋቂ ሊሆን እንደማይችል ጠማማነቱን ቢተው ነብር ዥንጉርጉርነቱን ቢለቅ ህወሓት ክፋታቸውን አይተውም።ስለዚህ ማስተዋል እኮ የራቀውን ለማቅረብ የቀረበውን ለማራቅ የሚያገለግል የልብ መነጽር ነው።ይህ ትግል ፋና ወጊ በሆነ ስር የሰደደ ተሞክሮና ለ27 ዓመት በኢትዮጵያ ሕዝብ በደረሰባቸው ስቃይ የተቀሰቀሰ በሕይወት የመኖር መብት ብሎም የወያኔ ግባተ መሬት የስርዓት ለውጥ ትግል ነው።

የወያኔ አምባገነን አገዛዝ በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ይወገዳል!!